19ኛ ዓመት ቁጥር 7
19th Year No. 7

ባሕር ዳር መጋቢት 1 ቀን 2006 ዓ.ም
Bahir Dar March 10,2014

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር
Unit price Birr

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 211 /2006 ዓ.ም**

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሠጣጥ፣የጠበቆች ምዝገባና ስነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ**

## Content

**Proclamation No.211/2014**

**The Amhara National Regional State Licensing, Registration and Controlling the Code of Conduct of Advocates Proclamation Revised Proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 211 /2006 ዓ.ም

### በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሠጣጥ፣የጠበቆች ምዝገባና ስነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅን ለማውጣት የወጣ አዋጅ

በሥራ ላይ ያለውን የጥብቅና ፈቃድ አሠጣጥ፣ምዝገባና የጠበቆች ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም አንዳንድ ድንጋጌዎች ሙያው ከሚጠይቀው አዳጊ የስምሪት ሽፋን ፍላጎት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No .211 /2014

### A Revised Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State Licensing, Registration and Controlling the Code of Conduct of Advocates Proclamation

WHEREAS, it as been found necessary to revise some provisions, found in effect of licensing, registration and controlling code of conduct of the advocates proclamation No. 75/2002, in relation to the demand of promoting to task assignment, which the profession requests;

በህግ ሙያ የሰለጠኑ ዜጎች ባገኙት እውቀት ራሣቸውን ጠቅመው የሚገኙበትን ህብረተሰብ በላቀ ስነ-ምግባር የሚያገለግሉበትን እድል መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ /49/ ንዑስ አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የጠበቆች ምዝገባና ስነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 211 /2006 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ማሻሻያ</u>

የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የጠበቆችን ምዝገባና ስነ-ምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፡-

ሀ/ የአዋጁ አንቀፅ /7/ እንደሚከተለው ሻሽሏል፡-

### 7. <u>ስለ ፈቃድ አይነቶች</u>

በቢሮው የሚሰጡ ሶስት አይነት የጥብቅና ሥራ ፈቃዶች ሲኖሩ እነርሱም የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ/ 2ኛ ደረጃ የጥብትና ሥራ ፈቃድ፣

ለ/ 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ፣

ሐ/ ልዩ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ፡፡

ለ/ የአዋጁን አንቀፅ /8/ ንዑስ አንቀፅ /1/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ /1/ ተተክቷል፡-

WHEREAS, it has been found relevant to create opportunity of lawyers, using themselves by <u>their Knowledge</u>; and rendering service with best conduct to the society.

Pursuant to, Article (49), sub-article 3/1/ of the Revised National Regional State Constitution, vested with its power, the council of Amhara Region issued this proclamation.

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "The Licensing, registration of advocates and controlling code of conduct proclamation, revised proclamation No.211/20014".

## 2. <u>Amendment</u>

The Issued proclamation N<u>o</u> of 75/2000 of the licensing, registration and controlling code of conduc of advocates proclamation is revised, by this proclamation as follows:

A. Article /7/ of the proclamation is revised as follows:

### 7. <u>Types of License</u>

There are three types of Licensing, which are rendered by the bureau:

A. Second class advocacy license
B. First class advocacy license; and,
C. Special advocacy license

B. Sub-article /1/ of Article/8/ is revocated and replaced by the following new sub-article/1/:

1/ ከታወቀ የህግ ትምህርት ቤት በኤል.ኤል.ቢ. ዲግሪ ተመርቆ "የመውጫ ፈተና" ያለፈ ወይም በህግ ሙያ ሰልጥኖ በዲኘሎማ የተመረቀና በሙያው ሁለት አመት የሠራ ወይም በሰርትፍኬት ተመርቆ በዳኘነት፣በዐቃቤህግነት፣ በሬጅስትራርነት፣ በህግ ኦፊሰርነት ወይም በነገረ-ፈጂነት ቢያንስ ለአምስት አመት ያገለገለ፡፡

1. Where he or she passes the institution's exit exam graduated by BLL degree from legally recognized school of law; or, has a diploma in law and has two years relevant experience; or, has a minimum of five years experience as a judge, public Prosecutor, registrar, legal officer or public pleader.

ሐ/ ከአዋጁ አንቀፅ /9/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀፅ /10/ የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ አንቀፅ መግባት ምክንያት ቀሪዎቹ አንቀፆች በአንድ ቁጥር ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡-

C. The following new Article/10/ is incorporated next to Article /9/ of the proclamation; due to the entrance of this additional Article, the remaining Articles are rearranged forward by one number:

10**. <u>ልዩ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ</u>**

1/ የህብረተሰቡን መብትና ጥቅም ለማስከበር ለሚሠሩና ለሠጡት አገልግሎት ምንም አይነት ክፍያ ሳይቀበሉ ነፃ የህግ አገልግሎት ለሚሠጡ ተቋማት ወይም ማዕከላት ቢሮው ነፃ የህግ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ይሠጣቸዋል፡፡

2/ ነፃ የህግ አገልግሎት በሚሠጥበት ጊዜ የሙያ ሥነ-ምግባርን ባለመጠበቅ ለሚፈፀሙ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች ፈቃዱን የመሠረዙና በአዋጅ ውስጥ የተቀመጡት ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ የተሠጠው ተቋም ወይም ማዕከል እና ግድፈቱን የፈፀመው ግለሰብ በህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**10. <u>Special Advocacy License</u>**

1. The Bureau shall render a special advocacy license that enables free service for institutions or centers, that works cause to respect the society's right and use; and, for those who render free legal supportive service, and do not take any payment for the rendering service;
2. Where legal free service is rendered, for faults of code of conduct, violating professional ethics; without prejudice to, revocating license and other administrational measures placed in the proclamation, the licensed institution or center and who violates, shall be accountable by the law,

3/ ተቋማቱ ወይም ማዕከላቱ እስከ ፍ/ቤት ድረስ በመሄድ ነፃ አገልግሎት የሠጧቸውን ግለሠቦችና ጉዳዩ ያስገኘውን ውጤት የያዘ ሪፖርት ለቢሮው የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

4/ ነፃ የህግ አገልግሎት የሚሠጣቸው ግለሠቦች ሊያሟሉት ስለሚገባቸው መረጃ፣ በነፃ ፈቃድ የሚሠጠውን አገልግሎት ጥራት እና የባለፈቃዶችን ሥነ-ምግባር የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል፡፡

3. <u>አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ባ/ዳር*
*መጋቢት 1 ቀን 2006 ዓ.ም*
*ገዱ አንዳርጋቸው*
*የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት*
*ርዕሰ መስተዳድር*

3. The institutions or centers shall have a duty to submit a report, that contains individuals, who are rendered a free service and the effect of the case, until they go to the court;

4. The Bureau shall issue particular directives that individuals, who are rendered a free legal service, shall fulfill information, for freely rendered service quality and code of conduct of the advocates.

3. **<u>Effective Date</u>**

This proclamation shall come into force as of the date of publication in the Regional Zikre-Hig Gazzeettee

Done at Bahir Dar,
This 10th day of March,2014
Gedu Andargachew
President of Amharа National Region